# አሥራት ምንድን ነው? ለምን ፥ እንዴትና ለማን ይሰጣል ?

አሥራትን አስመልክቶ ዝርዝር ማብራሪያን የሚሹ በርካታ ጥያቄዎች በተለያዩ ጊዜያት ደርሰውናል:: የዝግጅት ክፍላችንም ችግሩ የብዙኀን ምእመናን መሆኑን ተገንዝቧል:: ስለዚህም መሠረታዊ ጥያቄዎችን ለይቶ መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁንን በማነጋገር በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ቁ.1 እና ቁ.2 እትሞች ተከታታይ ጽሑፎችን ማቅረቡ ይታወሳል:: ለጉዳዩ ሊሰጥ ከሚገባ ትኩረት አኳያ በዚህኛው የሐመር መጽሔት የጥያቄዎቻችሁ መልሶች ዓምድ ከተጨማሪ ማብራሪያዎች ጋር አቅርበናል::

## አሥራት ምንድን ነው?

አሥራት ዐሥር፥ ዐሠረ፡አዐሠረ፡ ተዐሠረ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ዐሥር አደረገ፣ዐሥር ማድረግ፣ካሥር ተከፈለ፤ ዐሥር ተባለ ማለት ነው:: በዕብራይስጡ ወሱር፣ዐሣር፣በዐረብኛው ደግሞ ዐሽረ ይላል:: አሥራት በሰዋሰዋዊ ትርጉሙ፥ ዐሥረኛ እጅ፥ክፍል፤ ከአሥር አንድ ቀረጥ፣ ግብር መስጠት፣መቀበል ወይም መውሰድ ማለት ነው:: /ኪ.ወ.ክ ገጽ 700-701/:: በመንፈሳዊ ይዘቱም ክርስቲያኖች ከማንኛውም ገቢያቸው አሥረኛውን እጅ ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጡበትን ሥርዓት ያመለክታል:: /ዘሌዋ.27፥30-33፣ዘዳግ.12፥5-18፣14፥22-29፣ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ 18፥673-675 ፣ መጽ.ዲድ 7/:: ምእመናን አሥራታቸውን በከፈሉ ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር እነርሱንና ለእነርሱ ያላቸውን ሁሉ ይባርካል:: /ዘዳግ. 26፥13-15፣ሚል.3፥10/::

በመሠረቱ አሥራት የሚለው ሕጉ ሥርዓቱ በብሉያትም ሆነ በሐዲሳት ቅዱሳት መጻሕፍት ምንጩ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: ኦ.ዘፍጥ.14፥20፣ 28፥22:: ሥርዓቱም የእግዚአብሔር ሥርዓት ነው ብለን አሥራት የሚለውን ሕግ እንዳለ ተቀብለነው እንጂ በዘመነ ወንጌል ብዙ ጊዜ ከአሥር አንድ የሚለው ጉልቶ የሚታየው በአፈጻጸም ላይ በሙዳየ ምጽዋት ነው:: በትሩፋት መልክ ማድረግ ነው:: እንዲያውም የተወሰነውን መስጠት ብቻ ሳይሆን ከተወሰነው በላይ መስጠት ማለት ነው:: ሥርዓቱም የእግዚአብሔር ሥርዓት ነው ብለን አሥራት የሚለውን ሕግ እንዳለ ተቀብለነው እንጂ በዘመነ ወንጌል ብዙ ጊዜ ከአሥር አንድ የሚለው ጉልቶ የሚታየው በአፈጻጸም ላይ በሙዳየ ምጽዋት ነው:: በትሩፋት መልክ ማድረግ ነው:: እንዲያውም የተወሰነውን መስጠት ብቻ ሳይሆን ከተወሰነው በላይ መስጠት ማለት ነው::

## አሥራት የሚወጣው ከጠቅላላ የደመወዝ መጠን ወይስ ከተጣራ የደመወዝ ክፍያ?

ጉዳዩ የሕግ ጥያቄ ነው:: ክርስትና ሕገ ርትዕ አይደለም:: ሕገ ትሩፋት ነው:: ከመሠረቱ ይኽንን ማወቅ ያስፈልጋል:: ሕገ ርትዕና ሕገ ትሩፋት የተለያዩ ናቸው:: ይህን ጥያቄ ወደ ትሩፋት ሳይሆን ወደ ሕግ ገብቶ ነው የምናየው:: ወንጌል ሕገ ርትዕ አይደለችም:: ሕገ ትሩፋት ነች:: ኦሪት ደግሞ ሕገ ርትዕ ናት:: የተወሰነውን ነገር መፈጸም ብቻ:: ወንጌል ግን ከተወሰነው በላይ ሁሉ መሥራት ነው:: ስለዚህ ሕገ ትሩፋት ነው የምትባለው::

ከአሥር አንድ የኦሪት ነው:: የወንጌል ሕግ ደግሞ የተወሰነውን ብቻ ወይም አድርግ የተባለውንም ብቻ ማድረግ ሳይሆን አድርግ ከተባለውም በላይ ማድረግ ነው:: እና አሥራት የሚለው ከአሥር አንድ በአጭሩ በኦሪትም ቢሆን ከሚያገኘው ላይ ነው እንጂ ከማያገኘው ላይ አይከፍለ ውም:: አንድ ሰው ከሚያገኘው ላይ እንጂ ከማያገኘው ላይ አሥራት አይጠየቅም:: ሰውየው ተቀጥሮ የሚሠራ ደመ ወዝተኛ ከሆነ ከገቢው ላይ ነው:: ከጠቅላላ ደመወዙ ላይ ሳይሆን ከተጣራው ተከፋይ ገቢው ላይ ነው፤ አሥራቱን እንዲያወጣ የታዘዘው:: የኦሪቱ ሕግ አንድን ሰው ከማያገኘው ላይ አሥራት ክፈል አይለውም:: ከሚያገኘው ገቢ ላይ እንጂ::

## አሥራት የሚሰጠው ለማን ነው?

አሥራት ለማን እንደሚሰጥ በግልጽ ያልተረዱ ምእመናን በየቦታው የተለያየ ጥያቄ ያነሣሉ:: አስተያየትም ይሰጣሉ:: አንዳንዶች አሥራት የሚሰጠው ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው ይላሉ::ሌሎቹ ደግሞ የአሥራት ማኅበር አቋቁመው አሥራታቸውን እያሰባሰቡ ያጠራቅሙና በየገጠሩ ለተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት ጧፍ ዕጣን ያቀርባሉ:: የፈረሱትን ይጠግናሉ:: የተወሰነው ለንስሐ አባት መስጠት አለበት የሚሉም አሉ:: ለተቸገሩ ሰዎች መስጠት መርዳትም አሥራትን እንደማው ጣት ነው የሚሉም አሉ::

www.ethiopianorthodox.org

አሥራትን ለቤተ ክርስቲያን መስጠት ማለት እግዚአብሔርን ለሚያገለግሉ ካህናት መስጠት ማለት ነው:: በብሉይ ኪዳን ከሕዝቡ መካከል ቤተ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ በኩሮች ነበሩ:: በኩራት የሚባሉ የበኩር ልጅ ሁሉ ቤተ እግዚአብሔርን ማገልገል ግዴታ ስለሆነ ለቤተ እግዚአብሔር ይሰጥ ነበር:: ቤተ ሌዊ ለቤተ ክህነት ከተመረጠ በኋላ ግን ቤተሌዊ ለእና ቤተ አሮን ርስት አልባ እንዲሆኑ ተደርጓል:: ለምን? ርስታቸው እግዚአብሔር ነው:: ርስታቸው ሕዝቡ ነው:: በእርሻ ወይም በሌላ ሥራ እንዲተዳደሩ ሳይሆን ከሕዝብ በሚያገኙት አሥራት እንዲተዳደሩ፣ ርስታቸው ጉልታቸው አሥራት እንዲሆን፣ ሥራቸው በቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት እንዲሆን ተብሎ ተወስኗል:: ዘኁል. 18፥8:: ስለዚህ ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጠው ነገር ሁሉ ለካህናትም ነው የሚሰጠው:: የካህናት ማደሪያ ነው:: ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጠው ለካህንም ስለሆነ ለካህን ለብቻው የሚሰጥ የለም:: ለቤተ እግዚአብሔር መስጠትን ለካህን ከመስጠት ነጥሎ ማየት አይቻልም:: እንዲህም ሆኖ ግን ካህናቱም ቢሆኑ የአሥራት አሥራት ይከፍላሉ:: እንዲያውም ፈሪሳውያን ከቅመማ ቅመም ሳይቀር ይከፍሉ ነበር:: ማቴ.23፥23:: እነሱ ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጠውን አሥራት ይቀበላሉ:: ለቤተ እግዚአብሔር መሥዋዕት የሚሆነውን፣ ለዕጣን፣ ለመብራት የሚሆነውን የሚያስፈልገውን ሁሉ ካወጡ በኋላ የተረፈው የካህናቱ የዕለት ተዕለት መተዳደሪያቸው ይሆናል:: ስለዚህ ለቤተ እግዚአብሔር የተሰጠ አሥራት ለካህንም ተሰጠ ማለት ነው::

አሥራት የተሠራው በብሉይ ኪዳን ነው:: ለድሀ ተብሎ አይደለም:: ለቤተ እግዚአብሔር ተብሎ ነው:: የቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት የተሟላ እንዲሆን፣ ቤተ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ካህናት ተቸግረው አገልግሎቱ እንዳይጓደል፣ ካህናቱ በሌላ የመተዳደሪያ ሥራ ተሠማርተው አገልግሎቱን እንዳያስተጓጉሉ ወይም እንዳያጓድሉ ለእነሱ ማደሪያ የሚሰጥ እንጂ ለድሀ ተብሎ አይደለም:: አሥራት የተፈቀደው መጀመሪያ ሥርዓቱ የወጣው ለቤተ እግዚአብሔር ነው:: ለድሀ የሚሰጠው ለቤተ እግዚአብሔር ከሚሰጠው አሥራት የተለየ ነው:: ነገር ግን ከዚህ ውጪ ለድሆች የተለየ ነገር አለ:: ለምሳሌ በኦሪቱ ድሆች ምርት በሚሰበሰብበት ጊዜ ቃርሚያ እንዲለቅሙ በአጨዳ ጊዜ የወደቀ ነዶ እንዳይነሣ ይደረጋል:: በማሳም

ሆነ በውድማ ላይ የረገፈ እህል የወደቀ ነዶ የሚተወው ለድሆች ነበር።

በብሉይ ኪዳን ጊዜ ዋርሣ መውረስ /የሚችል ወንድም ሚስት መውረስ/ ሕግ ስለ ነበረ ችግረኛ ቤተሰብ ላይኖር ይችላል። ለምሳሌ አሁን በሐዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ድሀ አደጎችንና ባሎቻቸው የሞቱባቸውን መበለቶች አደራ በማለት አጠንክራ ታሳስባለች። በአሪቱ ግን በሐዲስ ኪዳን ያለው ዓይነት ችግር የለም። ዋርሣ መውረስ ስላለ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች የባሎቻቸው ወንድም ስለሚያገቧቸው እና ልጆቻቸውን ስለሚያሳድጉላቸውና በሐዲስ ኪዳን የሚታየው ዓይነት ችግር በዚያን ጊዜ አልነበረም። በሐዲስ ኪዳን ግን ዋርሣ መውረስ ስለሌለ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶችና ድሀ አደግ ልጆችን አደራ የሚባለው ለዚህ ነው። ስለዚህ ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጠው አሥራት ለድሆች የሚሰጠው ደግሞ ምጽዋት ይባላል።

ከአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ውጪ ለሌሎች የተቸገሩ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት መስጠት አሥራት እንደማውጣት አይቆጠርም። ለሌላ ቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ነገር መባዕ ነው የሚባለው። አንድ ምእመን ለፈለገው ቤተ ክርስቲያን መባዕ መስጠት ይችላል። አሥራቱን የሚሰጠው ግን አገልግሎት ለሚያገኝበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው። ምእመኑ ማንኛውንም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚቀበለው ከአጥቢያው ነው። ከዚህ በተረፈ በትሩፋት በመባዕ ለየትኛውም ቤተ ክርስቲያን ርዳታ መስጠት ይችላል።

ምእመናን ከሚያወጡት አሥራት የተወሰነው የንስሐ አባት ድርሻ ነው በማለት ለንስሐ አባታቸው የሚሰጡ አሉ የሚል ሃሳብ ተነሥቷል። እንግዲህ ደመወዝ በሌለበት ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱ የነፍስ ልጅ /የንስሐ ልጅ/ ለንስሐ አባቱ ይሰጣል። በደመወዝ የሚተዳደሩ ካህናት ከሆኑ ግን ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው አሥራትና መባዕ ለንስሐ አባትም ማለት ለካህናቱ ሆነ ማለት ነው። እንደውም በተጨማሪ በምእመናን ላይ እንዲከብዱ አያስፈልግም። ለካህናቱ ደመወዝ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ እየተከፈለ እንደገና ደግሞ ሌላ ተጨማሪ ደመወዝ ከምእመናን መቀበል አያስፈልግም።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጣም የተጠነቀቀውና እንደ ትልቅ ነገር የሚያየው ለምእመናን አለመክበድን ነው። ሐዋርያ፣ የምእመናን አባት ሆኖ ለምእመናን መክበድ እንደማይገባ አስተምሯል፤ በተግባር አሳይቷል። ካህናት በምእመናን ላይ ከከበዱ ትልቅ ችግር ያስከትላል። ምእመኑ ሲከብደው ሸክሙ የሚቃለልበት ሌላ አማራጭ ይፈልጋል። ከቤተ ክርስቲያን መራቅና መሸሽም ይፈልጋል። ካህናት በምእመናን ላይ ሳይከብዱ በጣም ተጠንቅቀ በአግባቡ መያዝ ያስፈልጋል። በእርግጥ ደመወዝ ሳያገኙ፣ ሳያርሱ፣ ሳይነግዱ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ካህናት ከሆኑ ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰባቸውን ማስተዳደር ስላለባቸው ምእመናን ሊረዷቸው ይገባል። አለበለዚያ ካህናቱ ከምእመናን ካላገኙ በስተቀር ቤተሰባቸውን ለማስተዳደር በሌላ ሥራ ላይ ከተሠማሩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይጓደላል። ስለዚህ ሌላው ምእመን አርሶ፣ ነግዶ፣ ሠርቶ ከሚያገኘው ቤተ እግዚአብሔርን ለሚያገለግሉት ካህናት የሚገባውን መክፈል አለበት። ይኸም በሰበካ ጉባኤ አማካኝነት ለቤተ ክርስቲያን መገልገያና ለካህናት ደመወዝ ይሰጣል።

ደመወዝ የሌለው ካህን ከተገኘ ለሚያገለግለው ካህን እያንዳንዱ ምእመን አቅም ያለው በገንዘቡ በመደጐም በሌላም ነገር የሚረዳ አለ። ለምሳሌ በገጠሩ ኢትዮጵያ ካህናቱ ደመወዝ ስለሌላቸው ምእመኑ /የንስሐ ልጁ/ እርሻውን፣ አረሙን፣ አጨዳውን፣ ሌላውንም ሥራ በመሥራት የንስሐ አባቱን ይረዳል። አንዳንድ ጊዜ ለምሳሌ በጐጃም በዓመት አንድ ጊዜ በደብረ ዘይት ዕለት ስብሰባ ይደረጋል። በንስሐ አባት ቤት ጠበል ጸዲቅ ይዘጋጅና በዚያ የሚሰበሰበው የንስሐ ልጅ የተቻለውን ስጦታ ያደርጋል። በጎንደር በቤጌምድር ስንሄድ የንስሐ ልጁ ካህኑን /የንስሐ አባቱን/ በእርሻ፣ በአረም፣ በአጨዳ በጉልበቱ ይረዳዋል እንጂ ካህኑ ከንስሐ ልጁ ገንዘብ አይጠብቅም። ምእመኑ ካህኑን በሚችለው አቅሙ ያገለግለዋል። ምእመኑ ለካህኑ ምንም ባያደርግለትም እንኳን ቄሱ የነፍስ አባት ነውና የንስሐ አባት ወይም መምህረ ንስሐ አልሆንህም አይለውም። ይህ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ካህን ሥዩመ እግዚአብሔር ነው። ምንደኛ አይደለም። ካህን ሹመቱ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ስለሆነ በከንቱ ያገኘውን በከንቱ፣ በጸጋ ያገኘውን በጸጋ የመስጠት ግዴታ አለበት።

በሌላ በኩል እናትና አባት የሞቱባቸውን ችግረኛ ልጆች ማሳደግ፣ የተቸገሩ ሰዎችን መርዳት አሥራት እንደ ማውጣት ሳይሆን የሚቆጠረው ብጽአት ነው የሚባለው። ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጠው ራሱን የቻለ ነገር ነው። ከዚያ በተረፈ አንድ ሰው ለድሆች በየወሩ ወይም እንደተገኘ በሆነው ጊዜ መስጠት አለበት።

በየቦታው እንደሚታወቀው ሕዝቡ ለድሆች ይሰጣል። አሥራቱን ደግሞ ለሰበካ ጉባኤ ለብቻ ይከፍላል። ለተቸገሩ ሰዎች ይረዳል ይመጸውታል። አሥራቴን ለቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ከፍያለሁ ብሎ የሚለምን ድሀ ዝም ብሎት አያልፍም። የሚችለውን ያህል ይሰጣል። ለድሆች የሚሰጠው የተለየ ነው። አንድ ሰው በየወሩ ከደመወዙ ወይም ከገቢው ላይ ለድሆች ይኸን ያህል እሰጣለሁ ብሎ ለይቶ መስጠት ወይም መክፈል ይችላል። ከአሥራቱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ለብቻ ማስቀመጥ ይችላል። ሕዝቡ ይህንን እየሁንም እያደረገው ይገኛል። ድሀን ያበላል፣ ያጠጣል፣ ያለብሳል። ለተቸገረ ይሰጣል። ስለዚህ ከሰበካ ጉባኤ ውጪ ወይም ለቤተ እግዚአብሔር ከሚከፍለው ሌላ ለድሆች የተወሰነ ከገቢው ላይ ተምኖ በወር ይኸን ያህል እሰጣለሁ ማለት ይችላል። ሳይተምንም እንዲሁ በትሩፋት መስጠት ይችላል።

## ነጋዴና ገበሬ አሥራት የሚያወጡት እንዴት ነው?

በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ጥያቄዎች ይነሣሉ። ነጋዴ አሥራቱን የሚያወጣው ከዕለት ገቢው ነውን? ጠቅላላው ወጪውንና ገቢውን አስልቶ ትርፍና ኪሳራውን ካሰበ በኋላ ነውን? በዕለት፣ በወር ወይስ በዓመት? ገበሬውስ? የሚሉና ሌሎችም ጥያቄዎች ይነሣሉ።

ብዙ ጊዜ አሥራት፣ በኩራት ቀዳምያት ተብሎ ሲወጣ የኦሪት ሕግ ነው። በአጭሩ ከላይ እንደተገለጠው የወንጌል ሕግ ከዚህ በላይ ማድረግ ነው። የወንጌል ሕግ ደግሞ የተወሰነ ነገር አይሆንም። እንደውም በወንጌል አንድ ሰው ያለውን ሁሉንም ንብረት ሸጦ ገንዘቡን ለድሀ ሰጥቶ መመንንም አለ። የወንጌል ሕግ የተለየ ነው።

በዚያን ጊዜ ለነጋዴ ግልጽ ሆኖ የተቀመጠ ነገር የለም። የሆነው ሆኖ ግን ወደ ወንጌል ስንመጣ ነጋዴዎች ትርፋቸውን ቆጥረው ሂሳቡን አስልተው ተምነው አሥራት መስጠት ብቻ ሳይሆን ለቤተ እግዚአብሔር የሚገባውን ከሰጡ በኋላ በመባዕ ከዚያ በላይ መስጠት አለባቸው። ገንዘባቸውን ቆጥረውና አስልተው ይኸን ያህል ገንዘብ ዕዳ አለብኝ ብሎ መክፈል አይደለም። በወንጌል ይህን ያህል ገንዘብ የእግዚአብሔር ዕዳ አለብኝ፤ ይህን ዕዳ ልክፈል አይባልም። ትሩፋት ነው መሥራት ያለበት። ቤተ ክርስቲያንን ያሠራል፤ ይሠራል። ድሆችን ይረዳል። የፈለገውን

www.ethiopianorthodox.org

# በየገጠሩ ያሉ የተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት

የመንግሥት ሠራተኛውም ሆነ ነጋዴው በአብዛኛው ያለው በከተማ ነው። አሥራቱን ለሚገለገልበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያውጣ ከተባለ በርቀት በየገጠሩና በየጠረፉ ያሉ የተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናትን እንዴት መርዳት ይቻላል? የሚል ጥያቄ አለ።

በአጥቢያ ከዚያም አልፎ በአገር ዓቀፍ ደረጃ ያለውን ችግር እያንዳንዱ ምእመን በተናጥል ሊፈታው አይችልም። ማዕከላዊ አሠራር ሊኖረው ያስፈልጋል። እያንዳንዱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማዕከል አለው። በወረዳ ከዚያም በአገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና አለን። ወደ ላይ በየደረጃው እስከ ቅዱስ ሲኖዶስ ድረስ አለ። ጠቅላላው ገቢ ከእያንዳንዱ ምእመን በአጥቢያ ደረጃ ከተሰባሰበ በኋላ ያንን በማስተንተን ማብቃቃት ነው። አሁን ያለው ችግር በአንዱ ቤተ ክርስቲያን የተትረፈረፈ ብዙ ገቢ ሲገባ ሌላው ደግሞ የሰሌት መቀደሻ ዕጣን፣ ጧፍ፣ ዘቢብ አጥቶ ሲቸገር ይታያል። የቤተ ክርስቲያንን ገቢ በአግባቡ ለመጠቀም በሚገባ የተደራጀና የተጠናከረ ማዕከላዊ አሠራር ቢኖር ይሄ ችግር አይፈጠርም ነበር። ምእመናን አሥራታቸውን ራሳቸው ለተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሰጡ ያደረጋቸውም ይኸው ነው።

እንዲህም ሆኖ ግን በግለሰብ ደረጃ ገንዘብ ያለው ባዕለ ጸጋ ምእመን ከአጥቢያው አልፎ በየገጠሩ የሚገኙትን ገዳማትና አድባራት በሚገባ እየረዳ ነው። በቡድን በኅብረት እየሆኑ በየገጠሩ በየጠረፉ ያሉትን የተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት የሚደግፉ፣ የፈረሰውን የሚጠግኑ፣ አዲስ የሚያሠሩ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዳይጓደል የሚያደርጉ ምእመናን በርካታ ናቸው። ታላቅ ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ።

ስለዚህ ምእመናን በአጥቢያቸው የሚከፍሉት አሥራት ሌላውን የትሩፋት ሥራ እንዳያደርጉ አይከለክላቸውም። በአጠቃላይ ግን ምእመናን በተናጠል የሚያደርጉት ርዳታ የሁሉንም ደሀ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ችግር ሙሉ በሙሉ አይቀርፍም። መሠረታዊ መፍትሔ የሚኖረው በማዕከላዊ ሁኔታ በተቀነባበረ መልኩ በድርጅታዊ አሠራር ነው። ይህንን ሁኔታ ምእመናንና ካህናቱ በቤተ ክህነት አማካኝነት በሚገባ ተወያይተውበት ቢወስኑ ማዕከላዊ አሠራር ለማምጣት አያስቸግርም ነበር። ካህናቱና ምእመናን በዚህ ጉዳይ ላይ መቀናጀት አለባቸው። ቤተ ክህነት ለምእመናንና ለካህናቱ በጉዳዩ ላይ ከአጥቢያ እንሥቶ የቤተ ክርስቲያንን ገቢ በማዕከላዊ ሁኔታ በሥርዓት ለመምራትና ለማስተዳደር ተከታታይ ዐውደ ትምህርት በመስጠት ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ካህናትና ምእመናን ጭምር አብረው በጋራ እንዲወስኑ ከተደረገ መልካም ነው። ካህናቱም በአብዛኛው ይኸንን ነገር የሚደግፉት ሃሳብ ይሆናል። በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ገቢ ሥርዓት ባለው ሁኔታ በአግባቡና በማዕከላዊ አሠራር ሆኖ የተዘጉና የተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት ጭምር በማዕከል ደረጃ እንዲደገፉ ይሁን ተብሎ ሃሳብ ቢቀርብ የእያንዳንዱ አጥቢያ ምእመን የሚቀበለው ጉዳይ ነው።

## ምእመናን አሥራታቸውን በአግባቡና በወቅቱ እንዲያወጡ ምን መደረግ አለበት?

ይህን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት ልንገነዘበው የሚገባ ጉዳይ አለ። ሕዝቡ የባሕል ግፊት አለበት። ችግሩ የባሕል ግፊቱን ማስታረቅ አለመቻላችን ነው። የባሕል ግፊቱ ምንድ ነው? በተለይ በቀጥታ አሥራት የሚለው ነገር በመጽሐፍ ቢኖርም በተግባር በተለይም በገጠሬቱ ኢትዮጵያ እንዲሁም በከተማው አልታየም።

ሕዝቡ ለቤተ ክርስቲያን በጣም ብዙ ነገር ያደርጋል። በአሥራት መልክ ለሰበካ ጉባኤ እንዲከፍል ሲጠየቅ ግን እንደ ትልቅ ዕዳ አድርጎ ይመለከተዋል። በግድ ነው የሚከፍለው። ምክንያቱም ልምዱ ከሥር ጀምሮ እየዳበረ ስላልመጣ ነው። ይሁን እንጂ ሕዝቡ ለቤተ ክርስቲያን ከአሥራ ሁለት ብር እና ከሃያ አራት ብር በላይ የበለጠ ብዙ ያደርጋል። ይህችኛዋ አዲስ ሕግ ሆና ስለ መጣችባቸው እንደ ትልቅ ዕዳ ይቆጥሯታል። ለቤተ ክርስቲያን ሲረዱ፣ ንዋያተ ቅድሳቱን ሲያሟሉ፣ አዲስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሲሠሩ፣ የፈረሰውን ሲጠግኑ፣ ድሀ ሲረዱ፣ ሲዘክሩ፣ ሲጋብዙ፣ ሲያለብሱ እጅግ ብዙ ነገር ሲያደርጉ አሥራት ከሚከፍሉት በላይ ያወጣሉ። ነገር ግን በዓመት የተወሰነውን አሥራት መክፈል ይከብዳቸዋል።

አሁን ከጊዜ በኋላ የከተማው ሰው እየለመደው የመጣ ይመስላል። በአብዛኛው የገጠሩ ሕዝብ ግን በባሕሉ ማርያም ባርኪ ተብሎ በየውድማው የመሬጌታ ይከፍላል። የገበዝ ይከፍላል። የዓመት መቀደሻ ይከፍላል። በተለይ በገጠሩ ማኅበረሰብ በአካባቢው ደብር የሚቀደሰው የዓመቱ በዓል ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ተለይቶ የሰበካው ሕዝብ አዋጥቶ የዓመት አስተ ዋጽኦ ይሰጣል። ከዚያ በተረፈ ደግሞ ራሱ እያወጣ መግበሪያ ይሰጣል። ይኸን እያደረገ አሥራት ለብቻ ክፈል ይባላል። ያንን ሁሉ እያደረገ አሥራት ክፈል መባል የለበትም።

ለማርያም ባርኪኝ፣ ለመሬጌታ፣ ለገበዝ፣ ለመቀደሻ ወዘተ በእህል መልክ የሚሰጠውን በሰበካ ጉባኤ ሒሳብ በአሥራት መልክ መያዝ ይቻላል። ከዚያ በኋላ በተለያየ ምክንያት መጠየቅ የለበትም። የተሰበሰበውን ለሚፈለገው ነገር በአግባቡ በሥርዓት እያወጡ መመደብ በሚገባ መጠቀም ይቻላል። ሕዝቡ የተሰበሰበው እህል በሰበካ ጉባኤ ገቢ ተይዞ በሚገባ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ላይ ሲውል ማየት አለበት።

በገጠር ገበሬው በየዓመቱ ምርቱን በውድማ በሚሰበስብበት ጊዜ የሚሠፈረው በቃለ ዓዋዲው እንደ አሥራት የሰበካ ጉባኤ ክፍያ ሆኖ ሊመዘገብለት ይገባል። ደንቡ የሚለው ይኸንን ነው። በገጠሬቱ ኢትዮጵያ ይህንን በአግባቡ ተግባራዊ የሚያደርገው ስለሌለ ግፊት ሲፈጥር ይታያል። ይህንን ለማስተካከል ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ በየሀገረ ስብከቱና በየወረዳው በሴሚናር መልክ በማስረዳት ግንዛቤ እንዲፈጠር እንደተደረገው ሁሉ ወደፊትም በተጠናከረ ሁኔታ መቀጠል ይኖርበታል። ስብከተ ወንጌሉም ተጠናክሮ ከተስፋፋ ምእመናን አሥራታቸውን ለምንና እንዴት ማውጣት እንዳለባቸው እየተረዱት ከእነሱ የሚጠበቅባቸውን በጊዜው ለማድረግ ይነሣሉ።

## ማጠቃለያ

በየትኛውም ዓለም የሚኖረው የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ምእመን ሁሉ ከአጥቢያ ጀምሮ እስከ ማዕከል ያለችውን ቤተ ክርስቲያን አንድ አድርጎ ማየት ይገባዋል። የገጠሬቱ ቤተ ክርስቲያን አለመኖር ማለት ማዕከላዊው የቤተ ክርስቲያን አካል አለመኖር ማለት ነው። ዳሩ ሲፈታ መሐሉ ዳር ይሆናል ይባላል። በእኛ በቤተ ክህነትም በምእመናንም ዘንድ ይህንን ተረድተንና አምነንበት የገጠሬ ወይም በጠረፍ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ስትዘጋ በዝምታ ማየት የለብንም። ያቺ ከዳር ያለችው የገጠር ቤተ ክርስቲያን ስትዘጋ መሐሉም ዳር እንደሚሆን አውቀን በጠቅላላው ምንም ገቢ የሌላቸውን አብያተ ክርስቲያናት በችግር ምክንያት

/ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል/

www.ethiopianorthodox.org

እንዳይዘጉ ማድረግ አለብን።

ለዚህ የተሻለው መፍትሔ የቤተ ክርስቲያንን ገቢ በማዕከላዊ ሁኔታ አደራጅቶ በሥርዓት በአግባቡ መምራትና ማስተዳደር ነው። ሌሎች አገሮች የሚያደርጉት እንደዚህ ነው። በአንዱ ገቢ ነው ሌላው አነስተኛ ገቢ ያለው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚተዳደረው። በአንዱ አጥቢያ ያሉ ምእመናን ቁጥራቸው አነስተኛ ሆኖ በሌላው አጥቢያ ብዙ ሺ ምእመናን ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ በጠረፍ አካባቢ ሃያና ሠላሳ ምእመናን ይኖራሉ። እነዚያ በአነስተኛ አቅማቸው ካህን ቀጥረው መገልገልና ማስገልገል ስለሚያቅታቸው ቤተ ክርስቲያኑም ይዘጋል። እነርሱም ወደ አረማዊነት ይመለሳሉ። በአንዱ አጥቢያ እጅግ የተትረፈረፈ ሀብት በአንድ በኩል ደግሞ ባዶ ሆኖ ይታያል። ይህን አስተካክለን በገጠሩ ቤተ ክርስቲያን ጭምር አገልግሎቱ ሳይጓደል የሚሰጥበት ሁኔታ ቢኖር መልካም ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ለማድረግ አቅሙም ችሎታውም አላት። የጎደለው ዘዴ ብቻ ነው። መቀናጀት ያስፈልጋል። ምእመናን ካህናትና በየደረጃው ያሉ የቤተ ክርስቲያን አካላት በቅንጅት በመወያየትና በጋራ በመሥራት የቤተ ክርስቲያናችንን የተጠናከረ አሠራር እግዚአብሔር እንዲያሳየን እንመኛለን። ✠

www.ethiopianorthodox.org